# የቤተ ክርስቲያን ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የመጠበቅ ሒደት በአድባራትና ገዳማት ሙዝየሞች ምቹ ኹኔታዎችና ተግዳሮቶች

**አለባቸው በላይ***

***Abstract***

*It is believed that the Ethiopian Orthodox Tewahido Church is the prime abode and source of Ethiopian history. In this respect, the Ecclesiastical objects which have been used in the church are good indicators of the diversified heritage it has. Before the establishment of museums in Ethiopia, the Church has been giving the service in various ways. This emanates from the long history and rich heritage that the church possesses. Than ever before, the Church is now paying due attention to the wellbeing of its heritage and started to establish museums in various parishes churches and monasteries. However, this practice of museum establishment has its own challenges and prospectus. To this end, this paper is targeted to assesses the existing situation in these church and monastery museums, identify the challenges and prospectus and in turn specify the better ways forward. The study is conducted bytaking four church museums as samples and using observation, interview, document study and related techniques as a data collection tools. The collected data of different types are sorted and analyzed using descriptive analysis technique. Accordingly, appreciating the growing process of museum establishment in various churches and monasteries, the study indicates the need for regulation which will enable the church conserve, research and promote its heritage better. In the meantime, the establishment of museums should be in line with the existing realities of the church or monastery concerned. This will make the church economically benefited apart from elongating the survival of it heritage.*

*Key words: Ethiopian Orthodox Tewahido Church; Church Museum; Heritage; Monasteries*

*ዲያቆን አለባቸው በላይ በደብረ ብርሃን ዩኒቨርስቲ የታሪክና ቅርስ አስተዳደር መምህር እና የትምህርት ክፍሉ ሓላፊ ናቸው።

## ፩. መግቢያ

ይኽ ወረቀት የቤተ ክርስቲያን ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን የመጠበቅ ሒደት በአድባራትና ገዳማት ሙዝየሞች በአኹኑ ሰዐት ያሉበትን ኹኔታ በመዳሠሥ ወደፊት መደረግ ያለባቸውን የመፍትሔ አቅጣጫዎች ያመላክታል። ጥናቱ ስምንት ክፍሎች ሲኖሩት ከክፍል አንድ እስከ ሦስት የጥናቱን ዐላማዎችና ሥነ ዘዴ ጨምሮ የሙዝየምን ጽንሰ ሐሳብና ዳራ በዐጭሩ የሚቃኝ ሲኾን አያይዞም የሙዝየምን ታሪካዊ አመጣጥ በዐለም ዐቀፍና በኢትዮጵያ የሚሉ ኹለት ክፍሎችን ይዳሥሣል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ሙዝየም የሚለው ቀጣዩ ክፍል ደግሞ በሥሩ ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶቿ፣ ሙዝየም ለቤተ ክርስቲያን ያለው ፋይዳ እና ሙዝየም በአድባራትና ገዳማት የሚሉ ጉዳዮችን ይተነትናል። በአምስተኛና ስድስተኛ የወረቀቱ ክፍል ለዚኽ ጥናት በናሙናነት የተወሰዱ የቤተ ክርስቲያን ሙዝየሞችን አጠቃላይ መረጃ እና በአድባራትና ገዳማት ሙዝየሞች የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በአጠቃላይ በአራት ተከፍለው ቀርበዋል። ክፍል ሰባት ምቹ ኹኔታዎችንና ተግዳሮቶችን የሚቃኝ ሲኾን ስምንተኛና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ ማጠቃለያና የወደፊት አቅጣጫዎችን ይዟል።

## ፪. የጥናቱ ዐላማዎች

### ፪.፩ ዐቢይ ዐላማ

በአድባራትና ገዳማት የሚገኙ ሙዝየሞችን ነባራዊ ኹኔታ በመዳሠሥ፣ ተግዳሮትና ምቹ ኹኔታዎችን መለየትና የወደፊት አቅጣጫዎችን መጠቆም ነው።

### ፪.፩ ዝርዝር ዐላማዎች

- ✓ በገዳማትና አድባራት ያለውን ሙዝየም የማቋቋም ሒደት መፈተሽ፤
- ✓ ከዚህ በፊት የተቋቋሙትን ሙዝየሞች ነባራዊ ኹኔታ መቃኘት፤
- ✓ ሙዝየሞቹን በማቋቋምና ማስተዳደር ሒደት ያሉትን ተግዳሮቶችና ምቹ ኹኔታዎች መለየት፤
- ✓ ለተሻለ የሙዝየም አገልግሎትና ቅርሶች ደህንነት ግብዐት የሚኾኑ ሐሳቦችን መጠቆም፤

## ፫. የጥናቱ ሥነ ዘዴ

ለዚኽ ጥናት የሚከተሉት የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ ዘዴዎች ተግባር ላይ ውለዋል።

## ፫.፩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

- ምልከታ:- አራት ሙዝየሞችን ምልከታ በማድረግ የሥዕል ብርሃነ (ፎቶግራፍ) መረጃዎችን መሰብሰብ ተችሏል::
- መጠይቅ:- የሙዝየሞቹን አስጎብኝዎችና በክልልና ዞኖች የባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች የሚሠሩ ባለሙያዎችን በጽሑፍና በቃል በመጠየቅ መረጃ ተሰብስቧል:: ክለሣ ድርሳናት:- ስለ ሙዝየም ምንነትና ታሪክ የሚያወሱ፤ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቅርስና ሙዝየሞች ላይ የተደረጉ የጥናት ወረቀቶችን እና በናሙናነት በተወሰዱት ሙዝየሞች የሚገኙ መጽሔቶችን በመረጃ ምንጭነት ተጠቅሟል::

### ፫.፩.፩ የመረጃ ትንተና

- ከላይ በተገለጹት መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች ገለጻዊ ዘዴን በመጠቀም የተተነተኑ ሲኾን፤ ምስሎችና ሰንጠረዥም በማብራሪያነት ጥቅም ላይ ውለዋል::

## ፬. የሙዝየም ጽንሰ ሐሳብና ዳራ

የሰው ልጅ በተለያዩ ዘመናትና ክፍለ ዐለማት በዘመን የቀደሙ ሰዎች የሠሯቸውንና ይገለገሉባቸው የነበሩ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ፋይዳ ያላቸውን ቁሳቁሶች የመሰብሰብ፤ የማጥናትና ጠብቆ የማቆየት ፍላጎትና ልምዱ ከፍተኛ ነው:: በተለይ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን በአንድ ቦታ በማሰባሰብ መጠበቅና መንከባከብ ከጀመረ ብዙ ዘመናት ተቆጥረዋል:: እነዚኽ ተግባራት ናቸው በጊዜ ሒደት አኹን ሙዝየም ብለን የምንጠራውን ተቋም እንዲፈጠር ያደረጉት::

የመጀመሪያው ሙዚየም ታል አለ አማርናህ (Tall al Amarina) በሚባል ቦታ በጥንታዊት በግብጽ በፈርዖን አኬንቶን (Pharaoah Akheaton) ፲፫፻፶፫-፲፫፻፴፮ ከክርስቶስ ልደት በፊት የተመሠረተ ሲኾን የዚኽ ሙዚየም ስብስቦች ለንጉሡ በወቅቱ ከነበሩ መንግሥታትና በሥሩ ተገዢ ከነበሩ ሕዝቦች የተበረከተ ነበር::

ሙዚዮን (Mouseion) የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በጥቅም ላይ የዋለው በእስክንድርያ (Alexander) ግብጽ በንጉሥ ቶልሚ አንደኛ (Ptolemy I) ከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስተኛው ምዕት ዐመት ነው:: ይኽ ቃል በጥንታዊ ግሪክ የዕውቀት አምላክ መቀመጫ ተብሎ የሚታመን የጣዖት ቤት መጠሪያ ስም ነበር:: ከዚያ ተያይዞ በጥንታዊቷ ሮም ይኽ ስያሜ የፍልስፍና ተቋማት መጠሪያም ኾኖ አገልግሏል:: በመካከለኛው ዘመን አብዛኛው የአውሮፓ ክፍል ወደ ክርስትና እምነት የመጣበት ወቅት ስለነበር በጥንታዊ

ግሪክና ሮማ የነበረው ሒደት መቀጠል አልቻለም፡፡[1]

ከ፲፭ኛ-፲፯ኛው መቶ ክፍለ ዘመን (መ.ክ.ዘ.) የአውሮፓ ሕዳሴ (Renaissance) እንቅስቃሴ አካል የነበረው የጥንት ዘመን የእደ ጥበብና ተያያዥ የሰው ልጅ ይገለገልባቸው የነበሩ ቁሳቁሶችን ማሰባሰብና ራሱን የቻለ ክፍል ሰጥቶ ማስቀመጥ (private cabinet) በአብዛኛው ይከናወን ነበር፡፡ በ፲፰ኛው መ.ክ.ዘ. ሙዝየሞች ጥንታዊ ቁሳቁሶችን በመሰብሰብ የሚጠብቅና ለሕዝብ ዕይታ የሚያቀርብ የሕዝብ ተቋም ወደ መኾን ተሻግሯል፡፡ ይኽ በተለይ በእንግሊዝና ፈረንሳይ በብዛት ይከናወን ነበር፡፡ በሌላ መልኩ በ፲፱ኛው እና ፳ኛው መ.ክ.ዘ. ባህላዊ ቁሶችን የያዘና ለሕዝብ ዕይታ ክፍት የኾነ ሕንጻ የሚል ትርጕም ሊይዝ ችሏል፡፡ አኹን ባለንበት በ፳፩ኛው መ.ክ.ዘ. ሙዝየም ባህላዊና ታሪካዊ ቁሶች ማሰባሰቢያ ወይም መገኛ ብቻ ሳይኾን የትምህርት እና ጥናትና ምርምር ማእከል በመኾን እያገለገሉ ነው፡፡ በተጨማሪም ከሙዝየም ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ  እንደ ዐለም ዐቀፍ የሙዝየም ካውንስል (ICOM) ዐይነት ተቋማትና ማኅበራት ተቋቁመው ብዙ የዐለም ክፍላትን ያካለለ ሥራ በመሥራት ላይ ናቸው፡፡[2]

# ፭. የሙዝየም ታሪክ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን

## ፭.፩ የሙዝየም ታሪክ በኢትዮጵያ

በ፲፱፻፴፯ ዐ.ም. የቅርስ ጥናት ጥበቃ ሥራ የመሣፍንቱንና የመኳንንቱን የወግና የክብር አልባሳት በቤተ መጻሕፍት ሕንፃ ውስጥ ለዐውደ ርእይ በማቅረብ የቅርስ እንክብካቤ የዘመናዊነት ቅርጽ ያዘ፡፡

በ፲፱፻፵፭ ዐ.ም. ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር የኹለትዮሽ የባህል ስምምነት ተፈርሞ በሰሜን ኢትዮጵያ በተከናወነው የአርኪዮሎጂ ሥራ የተገኙ ተንቀሣቃሽ ቅርሶችን መሠረት በማድረግ በአኹኑ የባንክ ክበቡ ብሔራዊ ቤተ መዘክር ፊት ለፊት ሥራ ጀመረ፡፡ በ፲፱፻፶፰ ዐ.ም. የታሪካዊ ቅርሶች አስተዳደር በሚል ስያሜ ተጠሪነቱ ለጽሕፈት ሚኒስቴር የኾነ ቅርሶችን በበላይነት የሚቆጣጠር የሥራ ክፍል ተዋቀረ፡፡ በ፲፱፻፷፯ ዐ.ም. የቅርስ ጥናት ጥበቃ መምሪያ በሚል ስያሜ በባህል ስፖርትና ወጣቶች ሚኒስቴር ሥር ኾኖ ተደራጀ፡፡ ፲፱፻፸፯ ዐ.ም. የቅርስ ጥናት ጥበቃ ድርጅት በሚል ስያሜ በባህልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር ተዋቀረ፡፡ በ፲፱፻፺፪ ዐ.ም. በባለሥልጣን ደረጃ ከፍ ብሎ የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን በሚል ስያሜ በባህልና ቱሪዝም ሚንስቴር ሥር ተደራጀ፡፡[3] ይኽንን ተከትሎ በተለያዩ ክፍለ ሀገራት ለምሳሌ፡- መቀሌ፣ ደሴ፣ ነቀምትና ጅማ

---

[1]https://www.britannica.com/topic/history-of-museums-398827 (accessed on 19/06/2017)

[2]ዝኒ ከማሁ፤

[3]Anais Wion, the n*ational archive and library of Ethiopia,* HAL archives-ouverts,2010,p.1

የሕዝብ ሙዝየሞች የማደራጀት ተግባር ተከናውኗል፡፡ በተለይ ባለፉት ፳፫ ዐመታት የብሔረሰብ ሙዝየሞች (Ethnographic Museums) በተለያዩ የብሔረሰብ ዞንና ወረዳ ከተሞች በመቋቋም ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ በበለጠ ግን በአድባራትና ገዳማት የሚቋቋሙ ሙዝየሞች ቊጥር ከፍተኛ ነው፡፡[4]

## ፭.፪ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ሙዝየም

ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ሙዝየም ግንኙነት (ሙዝየም ለቤተ ክርስቲያን ስላለው ፋይዳ) ከማየታችን በፊት ቤተ ክርስቲያኗ ያላትን የቅርስ ሀብት በዐጭሩ መዳሠሡ ጠቃሚ ነው፡

### ፭.፪.፩ ቤተ ክርስቲያንና ቅርሶቿ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታሪክ ባለጸጋ መኾኗ[5] ያላትን የቅርስ ሀብት በዐይነትና በመጠን እንዲበዛ አድርጓታል፡፡ በተለይም ከሌሎች አኃት አብያተ ክርስቲያናት በተለየ መልኩ በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት እግዚአብሔር የተመለከባትና በሐዲስ ኪዳንም ክርስትናን ለመቀበል ቀዳሚ ሀገር መኾኗ ለዚኽ ዐይነተኛ ማሳያ ነው፡፡ በዚኽ መሠረት በሀገራችን በኹሉም ሳይንሳዊ የቅርስ መሥፈርቶችና መለኪያዎች (ቋሚና ተንቀሳቃሽ፤የሚዳሠሡና የማይዳሠሡ) ቤተ ክርስቲያን የመሪነት ሚና እየተጫወተች እንዳለች በብዙዎች ዘንድ የታመነ ነው፡፡ በብሔራዊ ደረጃ ዕውቅና ካላቸው ቅርሶች ባሻገር በዐለም ቅርስነት የተመዘገቡ የሚዳሠሡና የማይዳሠሡ የሀገራችን ቅርሶችም አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ሀብታት ናቸው፡፡ እነዚኽን በገንዘብ የማይተመኑ ቅርሶች ከመጠበቅና ለትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር ሰፊ ሥራ የሚጠይቅ ሲኾን፤ይኽም በተለይ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ከመጠበቅ አንጻር ዕድሜ ጠገብ አድባራትና ገዳማት ሙዝየም ሊኖራቸውና ያላቸውም ሊጠናከሩ ይገባል፡፡

### ፭.፪.፪ ቤተ ክርስቲያንና ሙዝየም (ቤተ መዘክር)

ቤተ ክርስቲያን አሁን ሙዝየም ብለን የምንጠራው ተቋም ከመመሥረቱ በፊት በኹለት መልኩ በሙዝየምነት ታገለግል ነበር፡፡

*፩. ዕቃ ቤት* (Store Room) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳትን በመጠበቅና በመንከባከብ ረገድ በእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ቅጽረ ግቢ የሚገኙ ዕቃ ቤቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡[6] ፪. ቅዱሳት መካናት እንደ ቤት ውጭ/መስክ (Open Air) መካነ ቅርስ ያገለግሉ ነበር፤ አኹንም በማገልገል ላይ ናቸው፡፡ ከዚኽ አንጻር የላሊበላ

---

[4] ዝኒ ከማሁ፤

[5] Zelalem Getinet, ¨Potentials and challenges of Entoto Saint Mary Church to heritage tourism development¨. *Journal of Hospitality and Tourism Management,* Vol. 6(5), pp. 47-59, July, 2015.

[6] *Encyclopaedia Aethiopica,* Vol.5 p. 454

ውቅር አብያተ ክርስቲያናት እና ሌሎች በቅዱሳት ሥዕላት ያጌጡና ጥንታዊ የኪነ ሕንፃ ይዘት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማትን እንዲኹም ያሉበትን አካባቢ መልክዐ ምድራዊ ገጽታ ማየት ይቻላል። በዚኽ መነሻነት የተለያዩ ምሁራን ቅዱሳት መካናትን ሙዝየም (Open Air) ይሏቸዋል። ለምሳሌ:- መንግሥቱ ጎበዜ ላሊበላን የሕያዋን ዐለቶች ሙዝየም (A Museum of living rocks) ሲል መግለጹን በማሳያነት መውሰድ ይቻላል።[7]

በኢትዮጵያ የቤተ መዘክር (ሙዝየም) እና ቤተ መጻሕፍት (Library) በአንድ ማእከል መሰባሰብ የጀመሩበት ዘመን በውል ተለይቶ ባይታወቅም የታቦተ ጽዮን እንዲኹም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት ግማደ መስቀል በቤተ ክርስቲያኒቷ ሀብትነት መገኘታቸው ለዚኽም ቤተ ክርስቲያኒቷና ምእመናንን እምነትን ከመጠበቅና ከማስጠበቅ  አንጻር ለንዋየ ቅድሳቱም የሚሰጡት ትኩረት ከፍተኛ መኾኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅርሶች ጥበቃና እንክብካቤ ሥራን ቀደም ብላ እንደጀመረች መገመት አያዳግትም። ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙት አድባራትና ገዳማት የተሰባሰቡ ቅርሶችን በአንድ ማእከል ለማሰባሰብ ያደረጉት ጥረት በእጅጉ የሚመሰገን ቢኾንም በመቅደላው ጦርነት ወቅት እንግሊዞች ይኽንኑ ስብስብ በመቀራመት ዛሬ ሙዚየሞቻቸው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተንቀሣቃሽ ቅርሶች እንዲሞሉ ምክንያት ኾኗል። ከተዘረፉትና በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩት ቅርሶች መካከል ወንጌላዊ ቅዱስ ሉቃስ የሣለው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሥዕል  ቅርስ "ኵራተ ርእሱ" አንዱ ነው።

ኹሉም አብያተ ክርስቲያናት አድባራትና ገዳማት በየቅፅረ ግቢያቸው የግድ ሙዚየም (ቤተ መዘክር) የመገንባት ግዴታ የለባቸውም። የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ቤተ መዘክር (Ecclessastical Museum) መገንባት ያለባቸው በተመረጡ ዕድሜ ጠገብ በኾኑ አብያተ ክርስቲያናት ቅፅር ግቢ ውስጥ መኾን አለበት። ይኽም የሚሆነው ደግሞ ኹለት መሠረታዊ ኹነቶች ሲሟሉ ነው።

፩ኛ. በቂ የኾነ የተንቀሳቃሽ ቅርስ ክምችት ሲኖር፣
፪ኛ. ቤተ መዘክሩ የሚገኝበት ገዳም (ቤተ ክርስቲያን) በመንፈሳዊ ዕድገት ያደረገው አበርክቶ (ምሣሌ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም) ሲኖር ቤተ መዘክር (ሙዚየም) የሚቋቋመው ቅርሶችን ለመጠበቅ ለመንከባከብና እንዲኹም ከቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ አንጻር ምእመናንን በመንፈሳዊ ትምህርት ለመገንባት ታስቦ መኾን ይኖርበታል።

በመኾኑም በተገቢው ኹኔታ በአርማታና በብረት የተገነባ ግንብ እንዲኹም የማሳያ ሣጥኑ በምንም ዐይነት ኹኔታ ሊሰበርም ኾነ ሊሰነጠቅ የማይችል አስተማማኝ በኾነ

[7]Meabangistu Gobezie, Lalibela: A Museum of living Rocks, Addis Ababa, 2012.

የማሳያ ሣጥን (Show Case) መኾን ይገባዋል። እነዚኽ ኹለት መሠረታዊ የኾኑ ከግንባታ ጋር የተያያዙ ሥራዎች ባልተሠሩበት ኹኔታ ቅርሶችን በአልባሌ ጎጆ ወይም ያለ ጠንካራ የማሳያ ሣጥን በዐደባባይ ላይ ዘርግፎ ማሳየት ቅርሶችን ለዘረፋ ከማመቻቸት ውጭ ትርጉም አይኖረውም። ይኽም በቤተ ክርስቲያኒቷ ላይ አደጋ የሚጋብዝ ነው።

ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ተቋም እንደመኾኗ ከሃይማኖታዊ ተግባራት በዘለለ መንገድ ያዘነበለ ዐለማዊ መርሖ ሊኖራት አይገባም፤ ቱሪዝም ንግድ ነው። ከፍተኛ የሕዝብ ፍሰት የሚያስተናግድ እንደመኾኑ በጐና ጎጂ ተፅዕኖዎች አሉት። በተለይም ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት አንዳንድ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችን በመጋፋትና የሃይማኖት አባቶችን በገንዘብ በማማለል ረገድ ጎጂ ጎኑ አመዛኝ ነው። ስለኾነም በቤተ ክርስቲያን የሚቋቋም ቤተ መዘክር (ሙዚየም) ሃይማኖታዊ ፋይዳው ጉልህ ኾኖ መውጣት ይገባዋል። በተለይም ለሃይማኖት ተጓዦች (Pilgrimage tourist) የታቀደ መኾን ይኖርበታል።

በመኾኑም ሙዚየም አትራፊ ያልኾነ ትምህርታዊ ተቋም መኾኑ ከግምት ውስጥ ገብቶ የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል።

- ቅርሶችን በአግባቡ መሰነድ፤
- የተሰነዱ ቈጠራና ምዝገባ የተደረገላቸው ቅርሶች የተመረጡት ለዕይታ እንዲቀርቡ ማድረግ፤
- ከፊሎቹ ቅርሶች በዕቃ ቤት ኾነው እንክብካቤና ጥበቃ እዲደረግላቸው ማድረግ፤

## ፭.፪.፫ ሙዝየም ለቤተ ክርስቲያን ያለው ፋይዳ

የሙዝየም አስፈላጊነትና ፋይዳ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና እየተሻሻለ እንደመጣ በጥናታዊ ጽሑፉ ለማሳየት ተሞክሯል። በኢትዮጵያም ያለውን በተመሳሳይ መልኩ ቤተ ክርስቲያን ካላት የቅርስ ሀብት አንጻር ሙዝየም መገንባትና ማስፋፋት መቻል ይበል የሚያሰኝ ከመኾኑም በላይ የሚከተሉት ፋይዳዎች ይኖሩታል።

- ንዋያተ ቅድሳት ( Ecclesiastical Item) በመጠቀም በቤተ ክርስቲያኒቱ በዘመናት ሒደት ያለፈችበትን ሁኔታ ክርስቲያናዊ እሴቱን ባለቀቀ መንገድ ለአማኞች የጥንቱን ከአሁኑ ዕድገት ጋር በማነጻጸር ለማስተማር።
- የኢትዮጵያ የሥነ ጽሑፍ፣ የሥነ ሥዕልና ኪነ ሕንፃ ተያያዥ የኾኑ ባህላዊ ዕድገቶች የክርስትና ሃይማኖትን መሠረት በማድረግ ስለአደረገችው አበርክቶ ማስተማር።
- ዋጋ ሊተመንላቸው የማይችሉ መንፈሳዊ ቅርሶች (Spritual heritage) ጥንታዊ የኾኑ ንዋየ ቅዱሳትን በአንድ የተማከለ ቦታ ጥበቃና እንክብካቤ (conferratin) እንዲደረግላቸው መሥራት።

## ፭.፪.፬ ተንቀሳቃሽ የቤተ ክርስቲያን ቅርሶችን የመጠበቅ ታሪካዊ ዳራ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ዘመናዊ ቤተ መዘክር የመንበረ ፀሐይ እንጦጦ ማርያም ሙዚየም ነው፡፡ ይኽ ሙዝየም የተቋቋመው የዐዲስ አበባ መቶኛ ዐመትን ምክንያት በማድረግ በወቅቱ የተዋቀረው ኮሚቴ ባቀረበው ሐሳብ ሲኾን ከቤተ መዘክሩ ግንባታ ጋር ተያይዞ ቤተ ክርስቲያኑን ከዐዲስ አበባ ዋና ዋና መንገዶች ጋር የሚያገናኝ የአስፋበት መንገድም ተጠናክሮ እንዲሠራ ተደርጓል፡፡

ዛሬ ለዐለም ሕዝብ የአድናቆት/አግራሞት ምንጭ የኾኑ የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርሶች ብዙዎቹ ቤተ ክርስቲያን ጠብቃ ያቆየቻቸው ናቸው፡፡ ይኽንንም የጥበቃ ተግባር በዘመናት በኹለት ከፍሎ እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

፩. በሰላም ዘመን፡- በሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ቅርሶቹ እንዳይበላሹ ዐቅም በፈቀደ መጠን በመንከባከብ ዘመን ተሻጋሪ እንዲኾኑ አድርገዋል፡፡ በተጨማሪም ሌባ እንዳይሰርቃቸው፤ቃጠሎ እንዳይደርስባቸው በስውር በማስቀመጥ መታደግ ችለዋል፡፡
፪. በስደት/በመከራ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ብዙ የመከራ ዘመናት ቢኖሩም በዋናነት የሚጠቀሱ ኹለት ናቸው፡፡ እነርሱም የዮዲት ጉዲትና የአሕመድ ግራኝ ጦርነቶች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ብዙ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በነዚኽ ዘመናት የወደሙ ቢኾንም አባቶች በዘመኑ የተወሰኑትን ይዞ በመሸሽና በዱር በገደል በመሸሸግ መታደግ ችለዋል፡፡

ምሳሌ፡- ዝዋይ ገዳማት (ኦሮምያ ክልል ምሥራቅ ሸዋ)፤አሌልቱ ገብርኤል (ኦሮምያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን) ተጠቃሾች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ኹለት ኹኔታዎች ቤተ ክርስቲያኗ (በየዘመናቱ የተነሡ አባቶች) ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ማለትም ታቦታቱን፤ መጻሕፍቱን ዘመናት ተሻጋሪ እንዲኾኑ ያደርጉ የነበረው ጥረት ብቻ ሳይኾን የሚጠበቁባቸው መንገዶችም በጥበብ የተመሉ ናቸው፡፡

## ፭.፪.፭ ሙዝየም በአድባራትና ገዳማት

በአድባራትና ገዳማት ከ፲፱፻፹፱ ዐ.ም. (እንጦጦ ማርያም ሙዝየም) በፊት በኢትዮጵያ ሙዝየም በሚባል ደረጃ የተቋቋመና የተደራጀ የቅርስ ጥበቃ ሥርዐት አልነበረም፡፡ ከዚያ በኋላ ነው በዐዲስ አበባና በክፍለ ሀገራት ባሉ ገደማትና አድባራት የሙዝየም ግንባታ ትኩረት እያገኘ የመጣው፡፡ ይኽ በዋናነት ኹለት ምክንያቶች ይኖሩታል፤

 © ጥናትና ምርምር ማእከል ፣ ማኅበረ ቅዱሳን

፮. ስለ ቅርስ ትርጉምና ፋይዳ ያለው ግንዛቤ እያደገ መምጣት[8]
፯. የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች ቊጥር እያደገ መምጣት[9]ና ለቤተ ክርስቲያን ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ትኩረት መስጠት መጀመሩ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡[10]
ቤተ ክርስቲያን አኹን ላላት አበረታች የሙዝየም ግንባታ ጅማሮዎች የሚከተሉትን እንደ ማሳያነት ማንሳት ይቻላል፤ እንጦጦ ማርያም ሙዝየም፤ ዐዲስ ዐለም ማርያም ሙዝየም፤ አኵስም ጽዮን ሙዝየም፤ ላሊበላ ገዳም ሙዝየም፤ ሐይቅ እስጢፋኖስ ሙዝየም፤ ግምጃ ቤት ማርያም ሙዝየም፤ ጣና ገዳማት ዑራ ኪዳነ ምሕረትና አንኮበር መድኃኔ ዐለምን ጨምሮ በአኹኑ ሰዐት በአማራ ክልል ብቻ ሰላሳ የሚደርሱ ሙዝየሞች በአድባራትና ገዳማት ይገኛሉ፡፡[11]

## ፫. የጥናቱ መነሻ (ናሙና) ሙዝየሞች

የተወሰኑትን ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ደረጃቸውና አደረጃጀታቸው ቢለያይም ብዙ ጥንታውያን ገዳማትና አድባራት ሙዝየም ያላቸው በማጠናከር፤ የሌላቸው ደግሞ በማቋቋም ላይ ናቸው፡፡ ብዙዎቹ ሙዝየሞችም በይዘት (ስብስብ)ና አስተዳደራዊ ኹኔታቸው ተቀራራቢ ናቸው፡፡ ከዚኽ አንጻር ተመራማሪው የሚከተሉትን ሙዝየሞች በማሳያነት ተጠቅሟል፡፡

---

[8]Mengistu Gobezie, "Entoto St.Mary Museum: The Oldest Ethiopia Church Museum" *Journal of Ethiopian Church Studies*, 2010, No.1. p. 74.

[9]Encyclopedia Aethiopica, Vol.5. p. 454.

[10]በየደረጃው ያሉ የባህልና ቱሪዝም መሥሪያ ቤቶች በአድባራትና ገዳማት ያሉትን ቅርሶች ለመቈጠርና ለመከታተል ያሚያደረጉት ጥረተ አንዱ የማንቂያ ደወል ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡

[11]ግዛቸው መንግሥቱ፤ በዐማራ ክልል ባህል፤ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የቅርስ ቊጥጥርና መዝገባ ባለሙያ እና አብክመ ባህል ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ፤ የቱሪዝም ሀብት መረጃ፤ ቊጥር ፬፤ ፳፻፯ ዐ.ም.፣ ገጽ ፴፰፡፡

| ተ.ቍ | የደብሩ/ገዳሙ ስም | የሚገኝበት ቦታ | | | የተመሠረተበት ዐመተ ምሕረት | ምር መራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክልል | ዞን | ወረዳ | | |
| ፩. | ዑራ ኪዳነ ምሕረት | ዐማራ | ባሕር ዳር ዙሪያ | ባሕር ዳር ዙሪያ (ዘጌ) | ፳፻፯ ዐ.ም[14] | |
| ፪. | ሐይቅ እስጢፋኖስ | ዐማራ | ደ/ወሎ | ተሁለደሬ | ፳፻ ዐ.ም[15] | |
| ፫. | አንኮበር መድኃኔ ዓለም | ዐማራ | ሰ/ሸዋ | አንኮበር | ፲፱፻፺፯ ዐ.ም[16] | |
| ፬. | እንጦጦ ማርያም | ዐዲስ አበባ | ዐዲስ አበባ | ጉለሌ | ፲፱፻፸፱ ዐ.ም | |

ሰንጠርዥ ፩. ለጥናቱ በናሙናነት የተወሰዱ ሙዝየሞች ዝርዝር መረጃ ከላይ የተዘረዘሩትን ሙዝየሞች አጠቃላይ ኹኔታ ስንመለከት ሦስቱ ማለትም ዑራ ኪዳነ ምሕረት፣ ሐይቅ እስጢፋኖስ እና እንጦጦ ማርያም በአንጻሩ የተሻለ የኪነ ሕንፃ ይዘትና አደረጃጀት ሲኖራቸው አንኮበር መድኃኔ ዐለም ሙዝየም ግን በመቃረቢያ (ባለ ኹለት ክፍል ትንሽ ቤት) ሙዝየም የሚገኝና በዚኽም ምክንያት ብዙ ቅርሶችን ለዕይታ ማቅረብ አይችልም። ከቅርሶች አያያዝ አንጻርም በዚኽ ሙዝየም የሚገኙ ብዙ ቅርሶች ያሉበት ኹኔታ አሳዛኝና አሳሳቢ በሚባል ደረጃ የሚገለጽ ነው። ምክንያቱም ማስቀመጫ ቦታ በመጥበቡና በአግባቡ ባለመደራጀቱ ምክንያት መሬት ላይ ተቀምጠው የሚገኙ ቅርሶችም ስላሉ ነው።

ስለዚኽ የውስጥ አደረጃጀታቸውንም ስንመለከት በመጀመሪያዎቹ ሦስት ሙዝየሞች ቅርሶቹ የሚገኙባቸው መስተዋት የተገጠመላቸው የተለያየ ቅርጽና መጠን ያላቸው ቁም ሳጥኖች (show cases)፣ ስለ ቅርሶቹ ዐጫጭር ገለጻዎች (captions) ያሉ ሲኾን፤ ቍጥራቸው ውስንና በሚገባ ያልተዘጋጁ ቢኾንም በአንኮበር ሙዝየምም ቁም ሳጥኖችና ገለጻዎችን ማየት ይቻላል። አቀማመጣቸውም በአብዛኛው ክብ ቅርጽ የሠራና ለጎብኝዎች እንቅስቃሴ ምቹ የሚባል ሲኾን፤ የመንቀሳቀሻ ቦታው ስፋት በተለይ የሐይቅ እስጢፋኖስና አንኮበርን ስንመለከት ጠበብ ያሉና ትኩረት የሚሹ መኾኑን መመልከት ይቻላል። ምንም እንኳን ጥናቱ እንደ አጠቃላይ በቤተ ክርስቲያን ሙዝየሞች ላይ የሚያጠነጥን ቢኾንም ከላይ የተዘረዘሩትን ሙዝየሞችና ስብስቦቻቸውን በገለጻና በፎቶ በማስደገፍ በዚኽ ጽሑፍ ለማሳያነት ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው።

በአጠቃላይ የቅርስ ጥበቃና ትውውቅ እንቅስቃሴዎችንም ስናይ አበረታች ጅማሮዎች መኖራችውን መገንዘብ ተችሏል። ለምሳሌ: - በናሙናነት ከተወሰዱት አራት ሙዝየሞች

[12]አባ ገብረ ሥላሴ አበበ፤ የዑራ ኪዳነ ምሕረት ገዳም ሙዝየም አስጎብኝ።

[13]Hayiq St.Estefanos-Abune Iyesus Moa Communal Monastery Museum booklet, 2011, p.13.

[14]ቃለ ሕይወት ሀብተ ወልድ (ሊቀ ካህናት)፣ የአንኮበር ወረዳ ቤተ ክህነት ጸሐፊና የአንኮበር መድኃኔ ዐለም አስተዳዳሪ።

ከአንኮበር መድኃኔ ዐለም በስተቀር ሦስቱ የአብያተ ክርስቲያናቱን/ገዳማቱን ታሪክና ቅርስ እንዲኹም በሙዝየሞች ውስጥ የሚገኙ ቅርሶችን በመጽሔት መልክ በማዘጋጀት በኩል ያሉ እንቅስቃሴዎች እንዳሉ መመልከት ይቻላል::[15]

የሰው ኃይል አደረጃጀቱንም ስንመለከት ብዙዎቹ ሙዝየሞች አንድ ሰው (ሙዝየሙን በሓላፊነት የሚመራ እና አስጎብኚ) ብቻ ያላቸው ሲኾን እንጦጦ ማርያም ሙዝየም ግን የሥራ ድርሻቸው በግልጽ የተለየ ባይኾንም ከአንድ በላይ ሰዎች በሙዝየሙ ዙሪያ ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላል:: የትምህርት ዝግጅታችውና የቋንቋ ችሎታቸውም በዚያው ልክ ትኩረት የሚሻ ሲኾን፣ በዚኽ ረገድ አኹን አኹን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች[16] የሚሰጡ ዐጫጭር ሥልጠናዎች የችግሩን መጠን ከመቀነስ አንጻር ሚናቸው ከፍተኛ እንደሚኾን ይታመናል::

ከአስተዳደር መዋቅር ጋር በተያያዘ ያለውን ኹኔታ ስንመለከት በሀገረ ስብከት ደረጃ የቅርስ ቊጥጥር ክፍል ቢኖርም መዋቅሩ ወደ ወረዳና አጥቢያ የተዘረጋ ካለመኾኑም በላይ፣ ሙዝየሞችን ወይም በአጠቃላይ ቅርስን በሚመለከት ትኩረት ሰጥቶ የሚሠራ ክፍል ባለመኖሩ ምክንያት የሚያደራጀውም ይሁን የሚከታተለው ራሱ የደብሩ ወይም የገዳሙ አስተዳደር (ሰበካ ጉባኤ) ነው::

## ፮.፩ ተንቀሳቃሽ ቅርሶች በአድባራትና ገዳማት ሙዝየሞች

ምንም እንኳን በተለያዩ ዘመናት በገጠሙ ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ብዙ ቊጥር ያላቸው ቅርሶች ቢጠፉም፤ አኹንም ቤተ ክርስቲያኗ ያላት የተንቀሳቃሽ ቅርስ ሀብት በዐይነትም በብዛትም መጠነ ሰፊ ነው:: ከዚኽ አንጻር በብዙ ገዳማትና አድባራት ሙዝየሞች የሚገኙ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል::

**፮.፩.፩ ቅዱሳት መጻሕፍት** (የብራና):- ከ፲ኛው-፳ኛው መ.ክ.ዘ. የተጻፉ ገድላት፤ ድርሳናትና ከውጭ (ከግብጽና ሌሎች ሀገራት) መጥተው የተተረጐሙ ከሃይማኖታዊ ይዘታቸው ባሻገር ታሪካዊ፤ ሥነ ሕይወታዊና ተያያዥ መረጃዎች የያዙ መጻሕፍት ናቸው::

[15]Hayq St.Estefanos-Abune Iyesus Moa Communal Monastery Museum Booklet, 2011 (ሐይቅ እስጢፋኖስ) እና የሐመረ ኖኅ ዘጌ ዑራ ኪዳነ ምሕረት፡ የደብረ ሥላሴና መዕራፈ ቅዱሳን ዋሻ መድኃኔ ዐለም ገዳም ዐጭር ታሪክ (ዑራ ኪዳነ ምሕረት) የሚሉትን የሕትመት ሥራዎች በማሳያነት መጥቀስ ይቻላል::

[16]የጐንደር ዩኒቨርሲቲ በዐማራ ክልል በሚገኙ ገዳማትና አድባራት ላሉ የሙዝየም ሠራተኞች ከሚያዚያ ፴ እስከ ግንቦት ፫ በላሊበላ ከተማ የሰጠው የዐጭር ጊዜ ሥልጠና በአብነት የሚጠቀስ ነው::





*ሥዕለ ብርሃን ፩. ጥንታውያን የብራና ቅዱሳት መጻሕፍት (አንኮበር መድኃኔ ዐለም ሙዝየም)*





*ሥዕለ ብርሃን ፪. ጥንታውያን የብራና ቅዱሳት መጻሕፍት (ሐይቅ አስጢፋኖስ ሙዝየም)*

## ፮.፩.፪ ቅዱሳት ሥዕላት

በቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት ሥዕላትን መሣል ጥንት የተጀመረ ሲኾን፤ እነዚኽንም በሦስት ክፍሎች ማየት ይቻላል፡፡ እነርሱም፡- በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ (manuscript illuminations)፣ የግድግዳ ላይ ሥዕላት (wall paintings/murals) እና ተንቀሳቃሽ ሥዕላት (Icons) ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ሥዕላት በብዙ የቤተ ክርስቲያን ሙዝየሞች ማግኘት ይቻላል፡፡



*ሥዕለ ብርሃን ፫.  ቅዱሳት ሥዕላት (ሐይቅ እስጢፋኖስ ሙዝየም)*

## ፯.፩.፫ ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት (መስቀል፣ ጽንሐሕ፣ ጥላ፣ አልባሳት፣ ከበሮ፣ ጸናጽል፣ መቋሚያ ወዘተ.)



*ሥዕለ ብርሃን ፬. መስቀልና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት (ሐይቅ እስጢፋኖስ)*

**፮.፩.፬ ታሪካዊ ቁሳቁሶች፡-** የነገሥታት አልባሳት፣ ዘውድና ከተለያዩ ታሪካዊ ክስተቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ስብስቦች ይገኙበታል፡፡ምሳሌ፡-

- አንኮበር መድኃኔ ዐለምና እንጦጦ ማርያም - ከዐፄ ምኒልክና ከዐድዋ
- ሐይቅ እስጢፋኖስ - ከንጉሥ ሚካኤል ጋር እንዲኹም
- ጣና ገዳማት የሚገኙ ሙዝየሞች ደግሞ ከመካከለኛውና ጐንደር ዘመነ መንግሥታት ጋር የተያያዙ ተንቀሳቃሽ ቅርሶችን ማየት ይቻላል፡፡



*ሥዕል ብርሃን ፳. የነገሥታትና ካህናት ዘውዶች (ዑራ ኪዳነ ምሕረት)*

# ፯. ሙዝየሞችን በማቋቋምና ማስተዳደር ሒደት ያሉ ምቹ ኹኔታዎችና ተግዳሮቶች

## ፯.፩ ምቹ ኹኔታዎች

- ሙዝየምችን የመገንባት ጥሩ ጅምሮች፡-

ብዙ ጥንታዊያን አድባራትና ገዳማት ከሌላቸው ሙዝየሞችን ለመቋቋም፣ ካላቸው ደግሞ ለማጠናከር እያደረጉ ያለው ጥረት የሚያበረታታ ነው፡፡ ነገር ግን ግልጽ የኾነ የዐጭርና ረጅም ጊዜ ዕላማ ኖሯቸው የሚንቀሳቀሱ በቊጥር አናሳ ናቸው፡፡ ምክንያቱም አንዳንዶቹ ቅርሶቹን በአንድ ለማሰባሰብ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከጎብኝዎች

 © ጥናትና ምርምር ማእከል ፣ ማኅበረ ቅዱሳን

የሚገኘውን ገቢ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚቋቋሙ ስለሆነ ነው፡፡

- *ሀገራዊና ዐለም ዐቀፍ ኹኔታዎች፡-*

በሀገራችን በኢትዮጵያም ይኹን በዐለም ዐቀፍ ደረጃ ለቅርስ ጥበቃና ለሙዝየም ግንባታ እየተሰጠ ያለው ትኩረት መጠነ ሰፊ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የዐለም አቀፉ ሙዝየም ካውንስል (ICOM) እ.ኤ.አ. ከ፲፱፻፸፱/፺ ዐ.ም. ጀምሮ ግንቦት ፲ አካባቢ ዐለም ዐቀፍ የሙዝየም ቀን እንዲከበር እያደረገ ይገኛል፡፡

- *የሃይማኖት ቦታዎችን መሠረት ያደረገ የቱሪዝም ፍላጎት ማደግ፡-*

በአኹኑ ሰዐት በዐለም ዐቀፍና በኢትዮጵያውያን ጎብኝዎች የሚጎበኙ ገዳማትና አድባራት ቍጥር እየጨመረ መምጣቱ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህም በአንድ በኩል እየጨመረ የመጣውን የጎብኝዎች ቍጥር ማስተናገድ የሚችል የቅርስ አደረጃጀትና የመረጃ አሰጣጥ ሥርዐት መዘርጋት፤ በሌላ በኩል ከዘርፉ መገኘት ያለበትን ገቢ ማግኘት በሚያስችል መልኩ መንቀሳቀስ እንደሚስፈልግ አመላካች ነው፡፡



*ሥዕለ ብርሃን ፮. ጎብኝዎች ሐይቅ እስጢፋኖስ ሙዝየምን ሲጎበኙ*

- *የቤተ ክርስቲያን ቅርስና ታሪክ ላይ ትኩረት አድርጎ ጥናትና ምርምር የመሥራት ፍላጎት እያደገ መምጣት፡-*

በሀገራችን ባሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በቅድመ ምረቃና ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብራት በታሪክ፣ ቅርስ አስተዳደር፣ የከርሠ ምድር ቅርስ ጥናት (Archaeology)፣ የጥንታዊ ጽሑፎች ጥናት (Philology) እና መሰል ዘርፎች ያሉ ተመራማሪዎች፣ መምህራንና ተማሪዎች የብራና መጻሕፍትንና ተያያዥ ቅርሶችን በመረጃ ምንጭነት

ለመጠቀም ያላቸው ፍላጎት በከፍተኛ ኹኔታ በማደግ ላይ መኾኑ ሌላው አበረታች ጉዳይ ነው፡፡

## ፯.፪ ተግዳሮቶች

- በቤተ ክርስቲያን ቅርሶች አያያዝና ሙዝየሞች ግንባታ ዙሪያ ወጥ የኾነና የተማከለ መመሪያና ደንብ ያለመኖር፡-

ይኽም ኹሉም በየአቅጣጫው የራሱን አካሔድ የሚከተል ከኾነ ነገ የጋራና ወጥ የሆነ ሥርዐት መዘረጋትን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

- በአግባቡ ያልታቀደ፣ ያልተጠናና ሳይንሳዊ ያልኾነ የሙዝየም ግንባታ ፍላጎት ማደግ፡-

የብዙዎች አድባራትና ገዳማት ሙዝየም የመገንባት ዕቅድና ፍላጎት ከፍተኛ ነው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ዲዛይን ሠርተው ለመገንባት ገንዘብ በማሰባሰብ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይኽ ተግባር አበረታች ቢኾንም በአግባቡ ካልተጠናና  የአካባቢውን ነባራዊ ኹኔታ ካላገናዘበ ዘላቂና ውጤታማነቱ አጠያያቂ ይኾናል፡፡

- ቅርሶችን በአግባቡ የመጠበቅና የመንከባከብ ጉዳይ (ሙዝየም ከገቡ በኋላ) ፡-

ብዙዎቹ የቤተ ክርስቲያን ሙዝየሞች በአግባቡ ታቅደው የተተገበሩ ስላልኾኑ የውስጥ አደራጃጀታቸው ለቅርሶቹም ይኹን ለጎብኝዎቹ ምቹ ኹኔታን መፍጠር ያልቻሉ ናቸው፡፡ ይኽ ደግሞ ቅርሶቹን ለተለያዩ አደጋዎች ተጋላጭ ያደርጋቸዋል፡፡

- የአደረጃጀትና መረጃ አሰጣጥ ኹኔታው፡-

የብዙ ሙዝየሞች አደረጃጀት በአግባቡ የተጠናና የተዋቀረ አይደለም፡፡ ለምሳሌ፡- አስጎብኝ ብቻ ያላቸው ሙዝየሞች ብዙ ናቸው፡፡ እነዚኽም አስጎብኝዎች በአብዛኛው በዘመናዊ ትምህርት ያልገፉ ከመኾናቸውም በላይ ስለ ስብስቦቹ በቂ መረጃ ከመስጠትም አንጻር ውስንነቶች ይስተዋላሉ፡፡ ምክንያቱም ጎብኝዎቹ ከሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም ሊኾኑ ስለሚችሉና በዕድሜም ይኹን በሌሎች መሥፈርቶች የመረዳት ፍላጎትና ዐቅማቸው ስለሚለያይ የመረጃ አሰጣጥና አደረጃጀቱ ይኽን ግምት ውስጥ ማስገባት ስላለበት ነው፡፡ ከዚኽ በተጓዳኝ የውጭ ሀገራትን ቋንቋዎች (ለምሳሌ፡- እንግሊዝኛ) የሚያውቁ፤ ነገር ግን ያሉትን ቅርሶች ይዘትና ታሪክ በውል ያልተረዱና የተዛባ መረጃ የሚያስተላልፉም እንዳሉ ተመረማሪው በመረጃ መሰብሰብ ሒደቱ የታዘባቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለዚኽ በኹለቱም ወገን ያሉት ነገሮች ካልተስተካከሉ አጠቃላይ አገልግሎቱን ትርጕም አልባ ያደርገዋል፡፡

- የቅርሶች ደህንነት ጉዳይ፡-

ለዘመናት በዕቃ ቤት ከሌባ ተጠብቀው የኖሩ ቅርሶች አኹን ሙዝየም በመገንባቱ ምክንያት ለጎብኝዎችና ተመራማሪዎች ክፍት መኾናቸው፤ በአግባቡ ደኅንነታቸውን መጠበቅ የሚያስችል ሥርዐት ካልተዘረጋላቸው ለከፋ ዘረፋና ሕገ ወጥ ንግድ ተጋላጭ መኾናቸው የማይቀር ነው፡፡ በብዙዎቹ ሙዝየሞች ከጥበትና ከሚገባ ጎብኝ አንጻር ለዚኽ አደጋ ላለመጋለጣቸው ዋስትና የለም፡፡ በተጨማሪም ብዙዎቹ ቅርሶች ማስቀመጫ (ሸልፍ) ስለሌላቸውና አንዳንዶቹ ቢኖራቸውም በአግባቡ ስላልተሠሩ በቀላሉ ቅርሶችን አውጥቶ መውሰድ የሚያስችሉ ኹኔታዎች ይስተዋላሉ፡፡ በተጨማሪም ለሙዝየሙ ብቻ የተመደበ ዘበኛ (ጠባቂ) ስለሌለ ሲገቡም ይኹን ሲወጡ ፍተሻ አለመደረጉ የችግሩን ስፋት የበዛ ያደርገዋል፡፡

- የመዝናኛና መጸዳጃ ቤቶች አለመኖር፡-

ጎብኝዎች ጊዜ ወስደው ሙዝየም ውስጥም ይኹን በሙዝየሙ ዙሪያ ያሉትን ቅርሶች ማየት እንዳይችሉ በአቅራቢያው የመዝናኛ፣ መናፈሻና መጸዳጃ አገልግሎቶች አለመኖራቸው ሌላው ተግዳሮት ነው፡፡

# ፭.ማጠቃለያ እና የወደፊት አቅጣጫዎች

## ፭.፩ ማጠቃለያ

ሙዝየም ከጥንታዊ ግሪክ ዘመን ጀምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ በትርጉምና በዳራ እየሰፋ እንደመጣ ነገር ግን በየዘመናቱ የነበሩ ብያኔዎች አንድ ጥቅል ጭብጥ እንዳላቸው እሱም ቅርሶችን በአንድ በማሰባሰብ መጠበቅና ለትምህርት ምንጭነት መጠቀም የሚለው መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ከዚህ አንጻር ሀገራችን ኢትዮጵያ ያላት የቅርስ ሀብት ፈርጀ ብዙ መኾኑ የዐለም ዐቀፉን ትኩረት እየሳበ የመጣ ጉዳይ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም በሦስቱም ሕግጋት (በሕገ ልቡና፤ኦሪትና ሐዲስ) እግዚአብሔርን እያመለከች ያለች ሀገር መኾኗ ላላት የካበተ የቅርስ ሀብት ባለጸጋነት ምክንያት ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያኗ እምቅ እና ዕድሜ ጠገብ የተንቀሳቃሽ ቅርስ ሀብት ያላት ከመኾኑ በተጨማሪ የማይንቀሳቀሱና የማይዳሠሡ ቅርሶቿንም ጭምር ለማሳየትና ለማስተዋወቅ የሙዝየም አስፈላጊነትና ፋይዳዉን የጎላ ያደርገዋል፡፡ ከዚኽ አንጻር አኹን በብዙ ገዳማትና አድባራት ያለው የሙዝየም ግንባታ ጅምር አበረታች ነው፡፡ ነገር ግን ቅርሶችን ከማሰባሰብ ሙዝየሞችን ከማቋቋምና ከማስተዳደር አንጻር በዐቅድ (የዐጭርና የረጅም ጊዜ)ና ዐላማ ያለመንቀሳቀስ ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡ ለዚኽም መሠረታዊው ምክንያት

በቤተ ክርስቲያን አንድ ወጥ የኾነ መመሪያና መምሪያ አለመኖሩ መኾኑን ጥናቱ ያመለክታል፡፡

ወጥ የኾነ ሥርዐት አለመኖሩ ደግሞ ሙዝየም ያላቸውም ይኹን የሌላቸው አድባራትና ገዳማት ውስጥ የሚገኙት ተንቀሳቃሽ ቅርሶች ያሉበትን ኹኔታ አሳሳቢ ያደርገዋል፡፡ ከዚኽ በተጨማሪም ለጎብኚዎችና ተመራማሪዎች ምቹ ኹኔታዎች ባለመፈጠራቸው ምክንያት ቤተ ክርስቲያኗ ዕድሜ ጠገብ ታሪኳና የቅርስ ሀብቷ በአግባቡ እንዳይተዋወቅ እንቅፋት ከመኾኑም ባሻገር ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባውንም ገቢ እያገኘች አለመኾኑ ግልጽ ነው፡፡

ከዚኽ በተጓዳኝ ደግሞ አኹንም የሚመለከታቸው አካላት ችግሩን ከተገነዘቡና ለማስተካከል ቆርጠው ከተነሡ ብዙ ምቹ ኹኔታዎች አሉ፡፡ በአኹኑ ሰዐት ዐለም ዐቀፍም ይኹን በሀገር ደረጃ ለቅርስ ጥበቃ እየተቸረው ያለ ትኩረት መልካም መኾኑና ሊደግፉ የሚችሉ አካላት መኖራቸው ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የእንጦጦ ማርያም ሙዝየም በ፲፱፻፸፱ ዐ.ም. ሲሠራ በወቅቱ የነበረው የባህል ሚኒስቴር ድጋፍ ከፍተኛ ነበር፡፡[17] አኹንም ሳይንሳዊ በኾነ መልኩ ለሚደረግ የሙዝየም ማቋቋምና ማጠናከር እንቅስቃሴ የሚመለከታቸው የመንግሥት ሓላፊዎችና ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ሊወጡ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

## ፭.፪ የወደፊት አቅጣጫ (Recommendations)

በዚኽ ጥናት የተጠቆሙትንና ተያያዥ ተግዳሮቶችን በመቅረፍ ለቅርሶቹ ደኅንነት፣ ለጎብኚዎችና ተመራማሪዎች ምቹ ኹኔታን ከመፍጠር አንጻር ተመራማሪው የሚከተሉትን የመፍትሔ ሐሳቦች አቅርቧል፡፡

- ❖ ወጥ የኾነ መመሪያ ማዘጋጀት

መመሪያው እንደ ቤተ ክርስቲያን አድባራትና ገዳማት ሙዝየም እንዴት፣ መቼ፣ የት እና በምን መልኩ መገንባት እንደሚችሉ አቅጣጫ የያዘ ሊኾን ይገባል፡፡ መመሪያውን ለማዘጋጀት ከሚመለከታቸው የቤተ ክርስቲያኗና የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች (ባህልና ቱሪዝም) ባለሙያዎች ቡድን በማቋቋም ሊከናወን የሚችል ነው፡፡ መመሪያው በዋናነት የሚከተሉትን ነጥቦች ያያዘ መኾን ይኖርበታል፡፡

- ✓ የሚቻል መኾኑን የሚዳሥሥ ጥናት (feasibility study) መከናወን እንዳለበትና ማን ሊያከናውን እንደሚገባ፤
- ✓ ኪነ ሕንፃዊ ይዘት፣ ዐይነትና ብዛት፡- ለምሳሌ፡- በዐማራ ክልል ከሚገኙ የቤተ

[17] Mengistu Gobezie, “Entoto St.Mary Museum: The Oldest Ethiopia Church Museum” *Journal of Ethiopian Church Studies*, 2010, No.1. p. 74.

ክርስቲያን ሙዝየሞች በአንጻሩ የተሻለ የኪነ ሕንፃ ይዘት አለው የሚባለው የዑራ ኪዳነ ምሕረት ሙዝየም ነው፡፡ ምክንያቱም ይኽ ሙዝየም ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡ እነርሱም የቅርስ ማሳያ (exhibition hall)፣ ማከማቻ (store) እና ጽ/ቤት ናቸው፡፡[18]

- ✓ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተመራማሪዎች እስከምንና እንዴት ስብስቦቹን መጠቀም እንደሚችሉ በተለያዩ ጊዜያት በቤተ ክርስቲያን ቅርስና ታሪክ ዙሪያ ምርምር ያካሔዱ የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ምሁራን ኹል ጊዜ የሚያሰሙት አቤቱታ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትና ሌሎች ቅርሶችን ማየትና ለመረጃ ምንጭነት መጠቀም አዳጋች መኾኑን ነው፡፡[19] ስለዚኽ መመሪያው የተመራማሪዎችን መብትና ግዴታ ከማሳወቅ አንጻር ጠቀሜታው የጎላ ይኾናል፡፡
- ✓ ሳይንሳዊ የኾኑ የቅርስ አሰባሰብ፣ አደረጃጀት፣ አጠባበቅና ማሳያ ዘዴዎችን ከቤተ ክርስቲያኗ ትውፊትና ሥርዐት ጋር ባጣጣመ መልኩ ተዘጋጅቶ በመመሪያው መካተት ይኖርበታል፡፡

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትንና ተያያዥ ጉዳዮችን በጥልቀት የሚያስረዳ መመሪያ መዘጋጀቱ ተጠያቂነት ያለበትና የተማከለ የቅርስ ጥበቃ ሥርዐትም እንዲኖር ሚናው የጎላ ይኾናል፡፡

- ❖ **አስተዳደር ፦** የተዘጋጀውን መመሪያ ሊያስፈጽም የሚችል የአስተዳደር ሥርዐት መዘርጋት ሌላው መሠረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም መመሪያው መዘጋጀቱ በራሱ ችግሮችን ለመቅረፍና ሥር ነቀል ለውጥ ለማምጣት በቂ ስላልሆነ ነው፡፡ በተለያዩ ሀገራት ያሉ የተለያዩ ሙዝየሞች የተለያየ የአስተዳደር መዋቅር አላቸው፡፡ የመዋቅሩ ቅርጽ የሚወሰነው በሙዝየሙ ዐይነትና ይዘት ነው፡፡[20]

በአጠቃላይ የሙዝየም አስተዳደር አካላትን በኹለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡
፩. ቋሚ ሠራተኞች - የሙዝየሙ ሥራ መሪ (ኪዩሬተር) እና ሌሎች
፪. የሥራ ሕዋስ (committee) - የሙያ ስብጥር ያለበት
ከላይ የተጠቀሱት ኹለት አካላት የሚከተሉትን ዐበይት ተግባራትን ያከናውናሉ፡፡
ዋና ዋና የአርትዖት ተግባራትና የትኩረት አቅጣጫዎች፤

- ስብስቦቹን - መኖር ያለመኖራቸውንና ደኅንነታቸው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ማረጋገጥ፤

---

[18]ግዛቸው መንግሥቱ፣ በዐማራ ክልል ባህልና ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ የቅርስ ቊጥጥርና ምዝገባ ባለሙያ፡፡

[19]ይኽ ተግባር አባቶቻችን ለቅርሶች ደኅንነት ካላቸው ከፍተኛ ትኩረት የመነጨ ስለኾነ የሚደገፍ እንጂ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ነገር ግን ለምን እንደተከለከሉ ማስረዳትና ወደፊት ለምርምር የመረጃ ምንጭነት መጠቀም የሚያስችል ሥርዐት መዘርጋትን ይጠይቃል፡፡

[20]Grace Morley, *Fundamentals of Museology,* (Hyderabad, 1985).

- አገልግሎት አሰጣጡንና አጠቃላይ የሥራ እንቅስቃሴውን፤
- ገቢውን (የገንዘብ አሰባሰብና አስተዳደር ሥርዐቱን)[21] ወ.ዘ.ተ.

❖ ***የዐቅም ግንባታ ሥራዎች***[22] ፡- ከጥበቃ እስከ አስጎብኝዎች ያሉትን ከሙዝየሙና ከሙዝየሙ አገልግሎት ጋር ግንኙነት ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ያካተተ መኾን ይኖርበታል፡፡

❖ ***የማስተዋወቅ ሥራ፡-*** ምስል ወድምጽና የኅትመት ውጤቶችን በመጠቀም ሙዝየሞቹን የማስተዋወቅ ሥራም ወሳኝ ነው፡፡ ከዚኽ አንጻር የቤተ ክርስቲያኗን ልሣናት ከመጠቀም ባሻገር የመንግሥትና የግል የመገናኛ ብዙኀንንም መጠቀም አዋጭ ነው፡፡ በዚኽ ረገድ በአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን ሙዝየሞች የተጀመሩትን የኅትመት ሥራዎች (guide books) ለምሳሌ፡- በሐይቅ እስጢፋኖስ፣ በዑራ ኪዳነ ምሕረት ያሉትን ወደ ሌሎቹ ማስፋትና ማጠናከር አንዱ መንገድ ነው፡፡

❖ ***ደኅንነታቸውን የማስጠበቅ ሥራ፡-*** ቅርሶቹን ከውስጥና ከውጭ/የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ/ አደጋዎች መጠበቅ፡፡

❖ ***ለጎብኚዎች ምቹ ኹኔታን መፍጠር***[23]፡- የሀገር ውስጥም ይኹን የውጭ ሀገር ጎብኝዎች በተረጋጋ መንፈስ ሙዝየሙ ውስጥና በዙሪያው ያሉትን ቅርሶች ጎብኝተው እንዲሔዱ ሊሟሉ የሚገቡ መሠረታዊ ግብዓቶችን ማሟላት ያስፈልጋል:: በተለይም የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጎብኝዎች በሚበዙባቸው ጊዜያት በቂ ዝግጅት በማድረግ መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ፡- ሐይቅ እስጢፋኖስ ከመስከረም እስከ ጥር ባሉት ጊዜያት የጎብኝዎች ፍሰት ከፍተኛ ነው፡፡[24]

❖ ***የጸጥታ ጉዳይ፡-*** ብዙ ጎብኝዎች የሚያማርሩበት ሌላው ጉዳይ በአካባቢው የሚፈጠረው ግርግር በተለይ የውጭ ሀገር ጎብኝዎቸን ሥጋት ላይ ስለሚጥል በተረጋጋ መንፈስ መጎብኘትና መቆየቱን አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ለዚኽም ተገቢ የኾነ አቅጣጫ በማስቀመጥና ከአካባቢው የጸጥታ አካላት ጋር በጋራ በመሥራት ችግሩን መቅረፍ ይቻላል፡፡

---

[21] ሕጋዊ ደረሰኝና ግልጽ የኾነ የክፍያ መጠን ለመግቢያ (በዕድሜ/በዜግነት/በሥራ ኹኔታ)ና ካሜራ ለመጠቀም የሚሉትን ጉዳዮች እንደ የሙዝየሞቹ ነባራዊ ኹኔታ የክፍያ መጠኑን በመወሰን ለክትትል የሚመች ሥርዐት በመዘርጋት የሚከናወን ነው፡፡

[22] የዐቅም ግንባታ ሥራው አንድ ጊዜ ተከናውኖ የሚቆም ሳይኾን በተወሰነ የጊዜ ገደብ (ለምሳሌ፡- በየሩብ ዐመቱ) የሚከናወን ቢኾን ይመረጣል፤

[23] ሙዝየሞቹ ለጎብኝዎች (የሀገር ውስጥና የውጭ) ክፍት መኾን እንዳለባቸው ከታመነ የገዳሙን/ደብሩን ትውፊትና ሥርዐት ሥጋት ላይ በማይጥል መልኩ፤ መንገድን ማስተካከል፤ መቆያ ቦታዎች ማመቻቸት፤ መጸዳጃ ቤትና ሌሎች ተያያዥ አገልግሎቶችን ማሟላት የግድ ይኾናል:: ይኽን ተግባር በተለይ የሆቴልና ተያያዥ አገልገሎቶችን ገዳሙ በራሱ ማድረግ የሚችልበት መንገድ ከሌሎች አካላት ጋር በመነጋገር እንዲመቻቹ ማድረግ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ፡፡

[24] ብርሃነ ሕይወት (አባ)፣ የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ሙዝየም አስጎብኚ፡፡